የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 11
ADDIS ABABA, 20th December, 2023

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፩/፪ሺ፲፮

ለሰው ሀብት ልማት ኦፕሬሽን ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፉ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ………...………………………......ገጽ ፲፭ሺ፪፻፺፩

**Content**

Proclamation No.1301/2023

International Development Association Loan Agreement for Financing Ethiopia Human Capital Operation Ratification Proclamation ...…..Page 15291

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፩/ ፪ሺ፲፮**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ለሰው ሀብት ልማት ኦፕሬሽን ማስፈጸሚያ የሚውል ፴፯ ሚሊዮን ፪፻ ሺህ ኤስ.ዲ.አር. (ሠላሳ ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሐምሌ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ፫ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ጥቅምት ፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአካሄደው ፩ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

**PROCLAMATION NO. 1301/2023**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulated that the International Development Association shall provide to The Government of Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan an amount equivalent to Thirty Seven Million Two Hundred Thousand Special Drawing Rights SDR 37,200,000) for financing Ethiopia Human Capital Operation, was signed in Addis Ababa on 25th Day of July, 2023;

**WHEREAS,** the House of Peoples'Representatives of The Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified The said agreement at its 3rd year working period, 2nd ordinary session held on 12th Day of October, 2023;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ፩ . <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ “ለሰው ሀብት ልማት ኦፕሬሽን ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፉ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጸደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፩/ ፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሐምሌ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 7341-ET በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

## ፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፴፯ ሚሊዮን ፪፻ ሺህ ኤስ.ዲ.አር(ሠላሳ ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፲ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

## 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the “International Development Association Loan Agreement for Financing Ethiopia Human Capital Operation Ratification Proclamation 1301/2023”.

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Loan Agreement Number 7341-ET signed Addis Ababa on 25th Day of July, 2023 between The Government of Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is here by ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to Thirty Seven Million Two Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 37,200,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on its Publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, On this 20th Day of December, 2023**

**SAHLE-WORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**